# የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ተፈፃሚ የሚሆንባቸውን ፕሮጀክቶች ለመወሰን የወጣ መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 1/ 2001

## የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ተፈፃሚ የሚሆንባቸውን ፕሮጀክቶች ለመወሰን የወጣ መመሪያ

የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልጋቸው ፕሮጀክቶች ተለይተው እንዲመለከቱ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 አንቀፅ 5 የደነገገ ስለሆነ፣

በአካባቢ ጥበቃ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 295/1995 አንቀጽ 9 (3) መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

### 1. ሥያሜ

ይህ መመሪያ "የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 ተፈፃሚ የሚሆንባቸውን ፕሮጀክቶች ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 2/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልጋቸው የፕሮጀክቶች ዓይነቶች ዝርዝር

የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 በዚህ መመሪያ በተዘረዘሩት የፕሮጀክቶች ዓይነቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

### 3. የክልል መመሪያ

የክልል የአካባቢ መሥርያ ቤት በዚህ መመሪያ ላይ ተመስርቶ ሌላ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 4. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በምክር ቤቱ ሰብሳቢ ከተፈረመበት ቀን አንስቶ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ---- ቀን 2001 ዓ.ም.**

**የአካባቢ ምክር ቤት ሰብሳቢ**

| ተ.ቁ | የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚካሄድባቸው የፕሮጀክት ዓይነቶች |
|---|---|
| 1. | በፌዴራል መንግስት ፈቃድ ተሰጥቶአቸው የሚካሄዱ የማዕድን ልማት፣ |
| 2. | የውኃ ግድብ ግንባታ<br>• የግድቡ ከፍታ ከ15 ሜትር በላይ ወይም<br>• ግድቡ የሚይዘው የውኃ መጠን ከ3 ሚሊዮን ሜትር ኩብና በላይ ወይም<br>• ከ10 ሜጋ ዋት በላይ ኃይል የማመንጨት አቅም ያለው |
| 3. | የመስኖ ልማት<br>• ከ3000 ሄክታር በላይ |
| 4. | • የትራፊክ ፍሰቱ 1000 እና ከዚያ በላይ የሆነ (የዲዛይኑ ደረጃ ዲኤስ1፣ ዲኤስ2 እና ዲኤስ 3) መንገድ ግንባታ<br>• የባቡር መንገድ ግንባታ |
| 5. | ከሃይቅ ለንግድ በሚውል መጠን ዓሣ ማስገር |
| 6. | ለውጭ ገበያ የሚቀርብ የአትክልት፣ ፍራፍሬና የአበባ ልማት |
| 7. | የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ |
| 8. | የቆዳ ማልፋት ፋብሪካ |
| 9. | የስኳር ፋብሪካ |
| 10. | የሲሚንቶ ፋብሪካ |
| 11. | የማምረት አቅሙ 15 000 ኪሎ ግራም እና ከዚያ በላይ የሆነ የጎማ ፋብሪካ |
| 12. | የከተማና የኢንዱስትሪ የቆሻሻ ማስወገጃ ተቋም ግንባታ |
| 13. | የወረቀት ፋብሪካ |
| 14. | ዓመታዊ የዕርድ አቅሙ 100 000 እና ከዚያ በላይ የሆነ የቄራ ግንባታ |
| 15. | የሆስፒታል ግንባታ |
| 16. | መሰረታዊ የኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች ማምረቻ ፋብሪካ |
| 17. | ጥብቅ አካባቢ ተብሎ በሚጠራ ሥፍራ ውስጥና አቅራቢያ የሚተገበር ማንኛውም ፕሮጀክት |
| 18. | በቀን 24 000 ኪሎ ግራምና ከዚያ በላይ የሆነ የብረታ ብረት ማቅለጫና ማምረቻ ፋብሪካ |
| 19. | የአውሮፕላን ማረፊያ ቦታ ግንባታ |
| 20. | 25 000 ሊትሮ ወይም ከዚያም የበለጠ የሚይዝ የነዳጅ ማከማቻ ግንባታ |
| 21. | የኢንዱስትሪ ዞን ምስረታ |
| 22. | የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ |

**DIRECTIVE NO.1/ 2008**

**A DIRECTIVE ISSUED TO DETERMINE PROJECTS SUBJECT TO**

**ENVIRONMENTAL IMPACT ASSESSMENT**

**WHEREAS,** Article 5 of the Environmental Impact Assessment Proclamation No. 299/ 2002: provides for the determination of categories of projects requiring environmental impact assessment;

**NOW, THEREFORE,** this directive is issued in accordance with Article 9(3) of the Environmental Protection Organs Establishment Proclamation No. 295/2002.

1. **Designation**

This directive may be cited as the ''Directive No. 2/ 2008 issued to determine the Categories of projects subject to the Environmental Impact Assessment Proclamation No. 299/ 2002 "

2. **List of Types of Project Requiring Environmental Impact Assessment**

The Environmental Impact Assessment Proclamation No. 299/ 2002 shall be applied to the types of project listed under these directives.

3. **Regional Directive**

Any Regional Environmental Agency may issue another directives based on this directive.

4. **Effective Date**

This Directive shall enter into force as of the date signed by the Chairperson of the Council.

**Done at Addis Ababa, this ---- day of ------- 2008.**

**Chairperson of the Environmental Council**

| | Project Types Subject to Environmental Impact Assessment |
|---|---|
| 1. | Mine Exploration that is subject to Federal Government Permit |
| 2. | Dam and Reservior Construction<br>• Dam height 15 meter or more, or<br>• Reservior storage cpacity 3 million $m^3$ or more, or<br>• Power generation cpacity 10 MW or more. |
| 3. | Irrigation Development<br>• Irrigated area of 3000 ha or more |
| 4. | • Construction of Roads (Design Standard DS1, DS2 and DS3) with a traffic flow of 1000 or more<br>• Railway Construction |
| 5. | Taking Fish from Lakes on a commercial Scale |
| 6. | Horticulture and Floriculture Development for export |
| 7. | Textile Factory |
| 8. | Tannery |
| 9. | Sugar Refinery |
| 10. | Cement Factory |
| 11. | Tyre Factory with Production Capacity of 15 000 Kg/day or more |
| 12. | Construction of urban and industrial waste disposal facility |
| 13. | Paper Factory |
| 14. | Abattoir Construction with Slaughtering Capacity of 10 000/Year or more |
| 15. | Hospital Construction |
| 16. | Basic Chemicals and Chemical Products Manufacturing Factory |
| 17. | Any project planned to be implemented in or near areas designated as protected. |
| 18. | Metallurgical Factory with a Daily Production Capacity of Equal or More Than 24 000 Kilogram. |
| 19. | Airport Construction |
| 20. | Installation for the Storage of Petroleum Products with a Capacity of 25,000 Liters or more. |
| 21. | Establishment of Industrial Zone |
| 22. | Condominium construction |